# በግል ስፖንሰር የሚደረጉ ስደተኞችን ካናዳ ውስጥ መልሶ ስለማቋቋም



PSR

AMHARIC

## የመረጃ መጽሔት

ወደካናዳ በመምጣት ኑሮዎን መመስረት ይፈልጋሉ፤ ስለዚህም ማመልከቻዎ በካናዳ መንግስት ባለስልጣናት የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ተደርጎለታል:: ምናልባትም አሁን ከዚህ የሚቀጥለው ሂደት ምን እንደሆን እያሰቡ ይሆናል::ይሕ መጽሔት በማመልከቻዎት ላይ ውሳኔ ለመስጠት በቅደም ተከትል ከሚደርጉት ክንውኖች መሀከለ ቀጣዮቹ ሂደቶች ምን እንደሚመስሉ ከማሳየት ባሻገር ስለ ካናዳም ተጨማሪ መረጃዎች ይሰጥዎታል::



Citizenship and Immigration Canada
Citoyenneté et Immigration Canada

Canada

# ስለመልሶ መቋቋም ማወቅ ያለብዎ ነገሮች

እንደ ስደተኛ ለመልሶ መቋቋም መመረጥዎ በመልሶ መቋቋም ሂደቱ ውስጥ በጣም ወሣኝ እርምጃነው፤ ሆኖም የመጨረሻው እርምጃ አይደለም።

የመልሶ መቋቋሙን ዕድል ያገኙት በግል ስፖንሰር የተደረገ ስደተኛ [privately sponsored refugee (PSR) / réfugié parrainé par le secteur privé (RPSP)] ሆነው ከሆነ ወደካናዳ ለመጓዝ ስድስት ወራት ወይንም ከዛም የበለጠ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

ቀጣዩ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከዚህ በታች ተመልክቷል፦

## <u>የማመልከቻው ሂደት</u>

ማመልከቻዎ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሕክምና ምርምራ ማካሄድ ይኖርባችሁዋል፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ምንም ዓይነት ከባድ ወንጀል እንዳልፈጸሙና ለካናዳም ምንም ዓይነት የፀጥታ አደጋ የሚያስከትሉ አለመሆኑን ለማረጋገጥ የደህንነት ምርመራም ይደርግልዎታል። ይህ ከተከናወነ በሁዋላ ወደ ካናዳ መምጣት ይችሉ እንደሆን የካናዳ ባለስልጣን ይወስናል።

ከተመረጡ በኋላ የሕክምና ምርመራ እንዲያደርጉ እስኪጠየቁ ድረስ ብዙ ወራት ሊወስድ ይችላል።

የካናዳ የቪዛ ባለስልጣናት ማመልከቻዎን በመመርመር የሕክምና፣ የደህንነት እና የወንጀል ምርመራዎችን ማለፍዎን ይወስናሉ።

የሕክምና፣ የደህንነት እና የወንጀል ምርመራዎችን ካላለፉ በሁዋል እርስዎ ወደካናዳ መጥተው ኑሮ መጀመርን ላይመረጡ ይችላሉ።

- ወደካናዳ መጥተው መልሰው እንዲቋቋሙ ሲመረጡ እና ለመጓዝ እንደሚችሉ ሲታወቅ ካናዳ ለአለም ዓቀፉ የሰዎች ፍልሰት ድርጅት (አይኦኤም) [International Organization for Migration (IOM) / Organisation internationale pour les migrations (OIM)] ወይም በካናዳ መንግስት ለተቀጠረ ሌላ ድርጅት ይህንኑ ያስታውቃል።

አይኦኤም ወይም ሌላ ድርጅት ወደካናዳ ለመጓዝ እንዲዘጋጁ ድጋፍ ያደርጉልዎታል።

- አንዳንድ ሀገሮች ውስጥ ሰዎች ወደ ካናዳ ከመሄዳቸው በፊት ለዝግጅት የሚረዳ መረጃ የሚሰጥበት ዝግጅት ላይ እንዲሳተፉ ይጋበዛሉ። ይህም ዝገጅት ስለካናዳ በውጪ አገር የሚሰጥ መግለጫ (COA-ሲኦኤ) ተብሎ ይታወቃል። የሲኦኤ ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኘው ከካናዳ የዜግነትና ኢሚግሬሽን መስሪያቤት ሲሆን ፕሮጀክቱን በአለም ዙሪያ በተግባር ላይ የሚያውለው ደግሞ አይኦኤም ነው። እንኝህ የመረጃ መስጫ ዝግጅቶችም ከክፍያ ነጻ ናቸው። ከነኝህ ዝግጅቶችም ስለካናዳ አጠቃላይ ግንዛቤና ካናዳ ከደርሱ በሁዋላ ስለሚሰጡት የመልሶ ማቋዋቁዋም አግልግሎቶች ጠቃሚ መርጃ ያገኛሉ።

## ወደካናዳ መጓዝ

አይኦኤም ወይም ሌላ ድርጅት ወደካናዳ የሚጓዙበትን ቀን ይነግሩዎታል። እንዲሁም በረራውን ያዘጋጁልዎታል፤ እርስዎን ወደአውሮፕላን ማረፊያው ከማድረስ በተጨማሪም ወደአውሮፕላኑ ውስጥ እንዲሳፈሩይረዱዎታል፤ አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ የሚደረግ ሌላ ካስፈለገም ይተባበሩዎታል።

ፓስፖርት ወይም ሌላ ሕጋዊ የመጓጓዣ ሰነድ ከሌለዎ የካናዳ መንግስት ወደካናዳ መጓዝ የሚያስችልዎት ሰነድ ይሰጥዎታል።

ወደካናዳ የሚጓዙበት እና ለሕክምና ያደረጉትን ወጪ የካናዳ መንግስት በሚሰጥዎ ብድር ይሸፈናል።

ይህም ድጋፍ የሚደርግልዎት በብድር መልክ ስለሆን ሙሉውን ወጪ ለመንግስት መልሰው መክፈል ይኖርብዎታል። ካናዳ በደረሱ በ30 ቀናት ውስጥለጉዞዎም ሆነ ለሕክምና የተደረገውን ወጪ መልሰው መክፈል መጀመር ይኖርብዎታል። ብድሩ ቀስ በቀስ ሊከፈል ይችላል፤ እንደብድሩ መጠን ሙሉውን ወጪ አጠናቆ ለመክፈል ከአንድ እስከ ስድስት አምት የጊዜ ገደብ ይኖርዎታል።




ምርመራዎችዎን በሙሉ ካለፉና ሰነዶችዎ ዝግጁ ከሆኑ በኋላ አይኦኤም ወይም ሌላ ድርጅት ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ይወስዱዎታል፤ ወአውሮፕላን መሳፈሪያው እንዲገቡና ከአውሮፕላን ማረፊያው የስደተኛ ጉዳይ ባልስልጣናት ጋርም ጉዳይዎን እንዲጨርሱ ይረዱዎታል።

ራስዎን እና ቤተሰብዎን ለመደገፍ ካናዳ ውስጥ ስራ ለመፈለግና ለመስራት የሚችሉበት ዕድል አለ።

**በግል ስፖንሰር የሚደገፍ ስደተኛ ሆኖ ወደ ካናዳ መድረስ**

በግል ስፖንሰር የተደረገ ስደተኛ ሆኑ ማለት ካናዳ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች እርስዎን ካናዳ ካለው የኑሮ ዘይቤ ጋር ለማላመድ ፈቃደኝነት አሳይተዋል ማለት ነው፡፡ ይህ እርስዎን ስፖንሰር ያደረገዎ ቡድን ካናዳ ከደረሱ በኋላ ከሁለት አማራጮች አንዱ ቀድሞ እስከሚሆን ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል ወይም በገንዘብ አቅም እራስዎን እስኪችሉ ድረስ ሊደግፍዎ ሕጋዊ ውል ገብቷል። ስለዚህም ድጋፍ የሚያገኙት ከዚህ ቡድን እንጂ ከካናዳ መንግስት አይደለም።

ካናዳ ሲደርሱ ስፖንሰር አድራጊዎ አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ መጥተው ይቀበሉዎታል እንዲሁም ሀገሩን እንዲላመዱ ይረዱዎታል።

ማረፊያ የሚሆንዎት አፓርትመንት፣ ቤት ወይም ሆቴል የመሰለ መኖሪያ ስፍራ ይሰጡዎታል። ስፖንሰር አድራጊዎ እንዳዘጋጁልዎት የማረፊያ አይነት ይሄ በካናዳ የመጀመሪያ ሳምንታት ቆይታዎ በጊዜያዊነት የሚቀመጡበት ቦታ ወይም በዘላቂነት ለረጅም ጊዜ የሚኖሩበት ቦታ ይሆናል።

በተጨማሪም ምግብና ልብስም ይሰጡዎታል።

የካናዳን ሕይወት ወይንም አኑዋኑዋር በተመለከተ ያሉዎትን ጥያቄዎች ይመልሱልዎታል። ስፖንሰር አድራጊዎችዎ በተለያየ መልክ ይረዱዎታል። ለምሳሌም፤

የምግብ፣ የቤት ኪራይና የቤት ቁሳቁሶችን፣ እንዲሁም ሌሎች የዕለት ተዕለት የመኖሪያ ወጪዎችን በመሸፈን። እንደኤሌክትሪክና ውሃ የመሳሰሉ አገልግሎት ወጪዎችዎትን ሁሉ የሚከፍለው ይሄው ስፖንሰር ያደረገዎ ቡድን እንጂ የካናዳ መንግስት አለመሆኑን ማወቅ ይኖርብዎታል፤

ልብስ፤ የቤት ዕቃዎችና ሌሎችም ቁሳቁሶች። ከነዚህ ዕቃዎች ውስጥ አንዳንዶቹ አዲስ ሊሆኑ ሲችሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ከስፖንሰር አድራጊዎቹ መካከል በስጦታ የተገኙና ያገለገሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤

ካስፈለገዎት ከአስተርጓሚ ጋር በማገናኘት፤

የቤተሰብና (የአጠቃላይ ህክምናና) የጥርስ ሃኪም በመምረጥ፤

የሚኖሩበት ክፍለሀገር ለነዋሪዎች የሚሰጠው የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑና የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር (ሶሺያል ኢንሹራንስ ቁጥር ) እንዲያገኙ ማመልከቻ ማስገባት፤

ሕጻናትን ትምሕርት ቤት እንዲሁም ጎልማሶችን ለቋንቋ ስልጠና ማስመዝገብ፤

ከእርስዎ ጋር ተመሳሳይ የግል ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር ማስተዋወቅ፤

ስለባንክ አገልግሎቶች፡ ስለመጓጓዣ ወዘተ መግለጫ መስጠት፤

ስራ ለመቀጠር የሚያደርጉትን ጥረት መደገፍ። እንደተለመደው ከሆነ እንዲህ አይነቱ ድጋፍ እስከ 12 ወራት ብቻ ይቆያል፤ ከዚያ በኋላ የምግብ፣ የቤት ኪራይ፣ የመብራትና ውሃ፣ የልብስ እና የግብር (ቀረጥ) ክፍያዎችን ጨምሮ ወጪዎን መሸፈን የራስዎ ኃላፊነት ይሆናል።

የካናዳ ሕይወትዎትን ለመጀመር ያህል ስፖንሰር አድራጊዎችዎ የመነሻ ድጋፍ ቢያደርጉልዎትም፤ ፍላጎትዎ (ወይንም ከስፖንሰርዎ የሚጠብቁት የድጋፍ መጠን) ተጨባጭ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ሊሆን ይገባል። የካናዳ ሕይወትዎ በሚገባ የተቃና ይሆንልዎ ዘንድ ጠንክረው ለመስራት መዘጋጀት ይኖርብዎታል። የካናዳ የወደፊት ዕጣዎ በአብዛኛው በራስዎ ጥረት ይወሰናል።

## ከቤተሰብዎ ጋር መልሶ መቋቋም



በምርጫው ወቅት እርስዎና የትዳር ጓደኛዎ እንዲሁም በእርስዎ ስር የሚተዳደሩ ልጆች በአንድ ቅጽ ላይ ለማመልከትና ካናዳ አብራችሁ ለመምጣት እንደምትችሉ የካናዳ ባለስልጣናት አስታውሶዎት ሊሆን ይችላል።

ወደ ካናዳ ከመጓዝዎ በፊት በየትኛውም ጊዜ በጋብቻ ሁኔታዎ ላይ ምንም አይነት ለውጥ ቢኖር(ለምሳሌ ቢያገቡ ወይም ቢፋቱ) ወይም ልጅ ቢወልዱ አዲሶቹ የቤተሰበ አባላት በእርስዎ ማመልከቻ ውስጥ እንዲካተቱ ካናዳ ላለው ስፖንሠር አድራጊዎና ለካናዳ የኢሚግሬሽን ባለስልጣን መንገር አለብዎት። ስለዚህ የርስዎ ቤተሰብ አባላት በሙሉ በማመልከቻው ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ።

ካናዳ ላለው ስፖንሠር አድራጊዎና ለካናዳ የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ካናዳ ሄደው መኖር የሚፈልጉት ከመላው ቤተሰብዎ ጋር መሆኑን መንገር በጣም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ከእርስዎ ጋር ወይም ከሌላ ሰው ጋር የሚኖሩ የቤተሰብ አባሎችዎን (ሁሉንም ልጆችዎን፣ ወንድሞችዎንና እህቶችዎን፣ ወላጆች፣ የትዳር ጓደኛዎን ጨምሮ) በሙሉ መዘርዘር ያስፈልጋል። ለጊዜው ካናዳ መጥተው ኑሮ መመስረት ባይፈልጉ እንኳ በዝርዝሩ ውስጥ ሁሉንም የቤተሰብ አባላት ማካተት አስፈላጊ ነው። በማመልከቻዎ ውስጥ ያልተካተተ ማንኛውም ሰው ወደፊት ወደ ካናዳ መምጣት አይችል ይሆናል።

ወደ ካናዳ የሄዱ ዘመዶች ወይም የቅርብ ጓደኞች ካሉዎት የግል ስፖንሰርዎም ሆነ የካናዳ ባለስልጣናት እንዲያውቁት ማድረግ አለብዎት። ይሁንና በግል ስፖንሰር የተደረጉ ስደተኞች ስፖንሰር ካደረጋቸው ቡድን ድጋፍ በሚያገኙበት ሕብረተሰብ ውስጥ እንዲኖሩ ይጠበቃል።

## የስደተኛነት ሁኔታዎ




ለካናዳ፡ዜግነት፡ከማመልከትዎ፡በፊት፡ለምን፡ያህል፡ጊዜ፡ካናዳ፡እንደሚኖሩ፡ የተወሰኑ፡መስፈርቶችን፡ማሟላት፡ ይኖርብዎታል። አንዴ፡ እነዚህን፡ ግዴታዎች፡ ካሟሉ፡ ለካናዳ፡ ዜግነት፡ማመልከት፡ ይችሉ፡ ይሆናል።

ካናዳ፡ ሲደርሱ፡ በቋሚነት፡ ለመኖር፡ የሚያስችል፡ ሰነድ፡ ይሰጥዎታል። ይህ፡ ማለት፡ ደግሞ፡ በካነዳ፡ በቋሚነት፡ ለመኖር፡ ህጋዊ፡ ኖዎት። ትምህርት፡ ቤት፡ መሄድ፡ ወይም፡ መስራት፡ ይችላሉ።

ካናዳ ሲደርሱ ካናዳ በቋሚ ነዋሪነት የመኖር መብት እንዳለዎት የሚያሳይ መረጃ ይሰጥዎታል። ይህም ማለት ካናዳ የመቆየትና የመኖር ህጋዊ መብት አለዎት። ትምህርትቤት መሄድ ወይንም ሥራ መሥራት ይችላሉ።

## ካናዳ ውስጥ የት እንደሚኖሩ




ካናዳ ብዙ ከተማና መንደሮች እንዲሁም ፈጽሞ ሰው ያልሰፈረባቸው በርካታአካባቢዎችን የያዘች በቆዳ ስፋትዋም በዓለም ውስጥ ሁለተኛ ትልቅ ሀገር ነች። ብዙዎቹ ከተሞች የሚገኙት በካናዳ የደቡቡ ክፍል ነው። ብዙዎቹ ሰዎች የሚኖሩባቸው አካባቢዎችም በጣም የተራራቁ ናቸው፤ በአውሮፕላን ቢበሩ እንኳ አንዱ ቦታ ለመድረስ ረጅም ሰዓታት ያስፈልግዎታል። ለምሳሌ በቶሮንቶና በቫንኩቨር ከተሞች መካከል ያለው ርቀት ከ 4300 ኪሎ ሜትር ሲሆን በአውሮፕላን ከአራት ሰዓት በላይ ይወስዳል።

ስፖንሰር አድራጊዎችዎ በሚኖሩበት ከተማ ወይም መንደር እንዲኖሩ ይደረጋል። መኖሪያዎትን ካናዳ ውስጥ ወደሌላ ቦታ የመቀየር ነጻነትዎ የተጠበቀ ቢሆንም መጀመሪያ በኖሩበት ቦታ ቢያንስ አንድ ዓመት ያክል እንዲቆዩ እናበረታታዎታለን። ይህ ከስፖንሰር አድራጊዎችዎ ድጋፍ እንዲያገኙና ለእርስዎ ተብለው የተዘጋጁ አገልግሎቶች ተጠቃሚ መሆን ያስችልዎታል።

በፈቃድዎ ወይንም በምርጫዎ  መኖሪያዎትን ወደሌላ የካናዳ ግዛት መቀየር ከመርጡ ለተቀረው የስፖንሰርነት ጊዜ ስፖንሰር አድራጊዎችዎ ድጋፍ ላያደርጉልዎት ይችላሉ።  የግል ስፖንሰር አድራጊዎች እርስዎን ሊደግፉ የወሰኑበት ምክንያት በማኅረሰባቸው ውስጥ በመኖር ከነርሱ ጋርም በመስራት ራስዎን ይችላሉ ብለው በማመናቸው ነው። በካናዳ ውስጥ የትኛውም ቦታ የመኖር መብት ቢኖርዎም የግል ስፖንሰር አድራጊዎች እንዲደግፉዎ የሚገደዱት በማኅበረሰባቸው ውስጥ ለሚኖሩበት ለመጀመሪያው አንድ አመት ብቻ ነው። ግን እርስዎ ከተማውን ለመልቀቅ ከወሰኑ ስፖንሰር አድርጊዎችዎ ሊሰጡዎት የተስማሙበትን ድጋፍ ላይሰቱዎት ይችላሉ።

## ካናዳ ውስጥ የሚገኝ እርዳታ




እርስዎ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ለወንዶች፣ ለሴቶችና ለሕጻናት የሚሆኑ ብዙ ማኅበረሰባዊ ቡድኖችና   ማኅበሮች አሉ። እንደእግር ኳስ ወይም ዋና የመሳሰሉ ሊሳተፉባቸው የሚችሉ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች አሉ፤ እንዲሁም ቤተሰቡ ሁሉ በጋራ ሊያደርጋቸው የሚችል ብዙ እንቅስቃሴዎች አሉ። ጥቂቶቹ ነጻ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ይከፈልባቸዋል።

በአካባቢዎ ለአዲስ መጪዎች የሚደረጉ ስብሰባዎች ካሉ ለመከታተል ይሞክሩ። ይህ በማኅበረሰቡ ውስጥ ወዳጆች ለማፍራትና በአካባቢዎ ስለሚሰጡ አገልግሎቶች ለማወቅ ይረዳዎታል።

የራስዎን ማኅበረሰብ አባላት ማግኘት የካናዳ ሕይወትዎትን ለማቃናት ይረዳዎ ይሆናል፤ ሆኖም ከሌሎችም እርዳታ ለመጠየቅ አይፍሩ።

## የካናዳ ማኅበረሰብ



ካናዳ ውስጥ ወንዶችና ሴቶች እኩል ናቸው። ሁለቱም ተመሳሳይ መብት ሲኖራቸው በእኩል የአክብሮት ደረጃም ይስተናገዳሉ። የሁሉም አይነት ማኅበራዊ መደቦች፣ ባሕሎች፣ ዘሮችና ሃይማኖቶች ወንዶችና ሴቶች እርስ በእርስ አለገደብ ይቀላቀላሉ እንዲሁም በእኩልነት ይስተናገዳሉ።ካናዳ ውስጥ የሌሎችን በነጻነት የመናገር መብት እያከበሩ የራሶትን አስተያየት በነጻነት መግለፅ ይችላሉ።

በመላው ቤተሰብዎ ተከበው በነሱ መረዳትና መደገፍ ለምደው ይሆናል። ሆኖም አንዴ ካናዳ ከገቡ በኋላ ብቸኝነት ይሰማዎ ይሆናል፤ ሆኖም ብቻዎን አይደሉም። የሚያሳስብዎ ጉዳይ ካለ ስፖንሰርዎን ያነጋግሩ ወይም አንዱን የማኅበረሰብዎን አባል ያግኙ። እዚህ ካናዳ የጀመሩት ሕይወት የተሳካ እንዲሆን የሚረዱዎ ሰዎች አሉ።

## ቤተሰብዎን ስፖንሰር ማድረግ



አንዴ ካናዳ ውስጥ ከተደላደሉ በኋላ ሌሎች የቤተሰብዎ አባላት ወደ ካናዳ እንዲመጡ ስፖንሰር ማድረግ ይችሉ ይሆናል። ሆኖም ይህ ሂደት ረጅም ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ማወቅ ይኖርብዎታል፤ እንዲያውም እነዚህን የቤተሰብ አባላት ለብዙ አመታት ላያዩዋቸው ይችላሉ። የቤተሰብ አባል የሚባለው ደግሞ ወላጅ፣ አያት፣ የትዳር ጓደኛና በስርዎ የሚተዳደሩ ልጆች ናቸው። እነዚህ የቤተሰቦ አባላት ወደካናዳ ለመምጣት ባስገቡት ማመልከቻ ውስጥ መካተታቸውን እርግጠኛ ይሁኑ። ወንድሞች፣ እህቶች፣ አክስቶች፣ አጎቶች፣ የአጎትና የአክስት ልጆች እንዲሁም ለዐቅመ አዳም የደረሱ ልጆች ስፖንሰር መደረግ አይችሉም።

ካናዳ ውስጥ የት ቦታ እንደሚኖሩ ቤተሰብዎ በትክክል ማወቃቸውን እርግጠኛ ይሁኑ። የደብዳቤ መላኪያ አድራሻዎን፣ ያሉበትን ከተማና ክፍለ ሀገር ጨምሮ ማወቃቸውን እርግጠኛ ይሁኑ።

## ስራ ማግኘት







ምንም እንኳ በመጀመሪያው አመት የካናዳ ኑሮዎ እርስዎና ቤተሰብዎ የገንዘብ እርዳታ ቢደረግላችሁም በተቻለ መጠን ፈጥነው ስራ በማግኘት ራስዎን እና ቤተሰብዎን ማስተዳደር እንዲጀምሩ እንመክራለን: :የተሻለ እንግሊዝኛ ወይም ፈረንሳይኛ  መናገር በቻሉ መጠን ስራ የማግኘት ዕድልዎ እየጨመር ይሄዳል::

የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ፣ የኮሌጅ ዲፕሎማ ወይም የሙያ ምስክር ወረቀት ካለዎ ካናዳ ውስጥ ተቀባይነት ላይኖረው እንደሚችል ማስታወስ አለብዎት። ዲግሪዎ/የምስክር ወረቀትዎ ወይም ሌሎች የትምህርት መረጃዎችዎ ካናዳ ውስጥ ምን አይነት ተቀባይነት እንዳላቸው ወይንም እንደሌላቸው  የክፍለ ሀገር መንግስት ወይም ደረጃ መዳቢ አካል ይወስናል።

ሀገር ቤት ለሚገኙት ቤተሰብዎችዎም ገንዘብ መላክ ይፈልጉ ይሆናል። ይህንን ለማድረግ ነጻ ነዎ፤ ይሁንና አብዛኛዉን ጊዜ ስደተኞች ራሳቸውን አስተዳድረው ከዚያ በኋላ ደግሞ ገንዘብ ተርፏቸው ወደቤተሰብ ለመላክ አስቸጋሪ ሆኖ ያገኙታል። ያስታውሱ፤ ካናዳ ከሚያጋጥምዎ አዲስ ሕይወት ጋር ለመለማመድ ጊዜ ይወስዳል።

## ወጪዎች


ካናዳ ሲደርሱ ከግል ስፖንሰር አድራጊዎችዎ የገንዘብ ድጋፍ እስከ 12 ወራት ለሚደርስ ጊዜ ይደረጉልዎታል። ይህ ድጋፍ ካበቃ በኋላ የምግብ፣ የቤት ኪራይ፣ የመብራት የውሃ፣ የልብስና  የግብር ክፍያዎችን ጨምሮ ወጪዎችዎን መሸፈን የራስዎ ኃላፊነት ይሆናል። ገንዘብዎን እንዴት በአግባቡ እንደሚጠቀም መማር በጣም ጠቃሚ ነው።

## ትምሕርት ቤት



ልጆችዎ የመጀመሪያም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርት ቤቶችን እንዲከታተሉ ክፍያ መክፈል አይኖርብዎትም። እድሜያቸው ከስድስት እስከ አስራ ስድስት የሆኑ ልጆች (18 አመት አካባቢ)  በሙሉ ትምሕርት ቤት መሄድ አለባቸው። ይህ ሕግ ነው። በብዛት ተማሪዎች የምርቃት ዲፕሎማ እስኪያገኙ ድረስ ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን ይከታተላሉ።  የኮሌጅና ዩኒቨርሲቲ ትምህርት ግን ገንዘብ ያስከፍላል። ስለዝህም ሁለተኛ ደረጃ ትምሕርታቸውን ከጨረሱ በኋላ መክፈል የሚችሉ ከሆነ ወደ ዩኒቨርሲቲ ወይም ኮሌጅ ይገባሉ።

## የጥርስ እንክብካቤ



የጥርስ ሃኪም ማየት ካለብዎ እርስዎ ወይም ስፖንሰርዎ ሂሳቡን መክፈል ይኖርባችኋል።

## ምግብና ውሃ



እያንዳንዱ ቤት የራሱ የሆነ በቧምቧ የሚፈስ ሙቅና ቀዝቃዛ ውሃ አለው። በየትኛውም የቀን ወይም የማታ ክፍል ውሃ ሊያገኙ ይችላሉ። ማድረግ ያለብዎ መክፈትና ተጠቅመው ሲጨርሱ መዝጋት ብቻ ነው።

ካናዳ ውስጥ ከተለያየ ባሕል የመጡ ሰዎች ይኖራሉ። ብዙውን ጊዜ የሚበሏቸው እንደ ሩዝ፣ ዳቦ፣ አታክልቶች፣ ቅመማ ቅመሞች፣ ምስርና ዶሮ የመሳሰሉትን በአካባቢዎ ባለው የሸቀጥ ሱቅ ሊያገኙ ይችላሉ። ካናዳ ብዙውን ጊዜ በተለመደው የሸቀጥ ሱቆችም የማይገኙ እንደፍየል ስጋ የመሳሰሉ ለየት ያሉ ምርቶችን የሚሸጡ ንግድ ቤቶችም አሏት።

## ሃይማኖት






ካናዳ ውስጥ ብዙ ሃይማኖቶች ይገኛሉ። የራስዎን ሃይማኖት በነጻነት መከተል ይችላሉ። ሌሎች ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ሰዎችን እንዲያከብሩም የካናዳ ሕግ ያስገድዳል። ሃይማኖትዎን እንዲቀይሩ አይጠየቁም ወይም አይገደዱም።  የሃይማኖት ነጻነት የካናዳ አንዱ መሰረታዊ መብት ነው።

## የአየር ጠባይ

በካናዳ በርካት ክፍሎች አራት ወቅቶች አሉ፤ እነዚህም ፀደይ፣ በጋ፣ በልግ እና ክረምት ናቸው። ካናዳ በጣም ትልቅ ሀገር ነች፤ ስለዚህም በእያንዳንዱ ወቅት ያለው የአየር ጠባይ አንዱ ክፍለ ሀገር ከሌላኛው ሊለያይ ይችላል። ፀደይ (መጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት) በብዙው የካናዳ ክፍል ዝናባማ ወቅት ነው፤ ስለዚህም የአየር ጠባዩ ቀዝቀዝ ሊል ይችላል።

በበጋ ደግሞ (ሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ) በአብዛኛው  ክፍላተ ሀገራት የአየር ጠባዩ በጣም ሞቃታማ ነው። ቀን ላይ የሙቀቱ መጠን ብዙውን ጊዜ ከ20 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በላይ ሲሆን አንዳንዴም ከ30 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሊበልጥ ይችላል። በልግ ላይ ደግሞ (መስከረም፣ ጥቅምትና ህዳር) የአየር ጠባዩ ቀዝቀዝ ሲል በጣም ዝናባማም ሊሆን ይችላል። በክረምት ወራት (ታሕሳስ፣ ጥርና የካቲት) በአብዛኛው የሀገሪቷ ክፍል ቀንም ሆነ ማታ የአየር ጠባዩ ከ ዜሮ ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ሆኖ ይቆያል፤ ከኔጋቲቭ 30 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች ሁሉ ሊወርድ ይችላል። የክረምት ወቅቶች በጣም ቀዝቃዛ ሊሆኑ ይችላሉ፤በአግባቡ መልበስ ይኖርብዎታል።









## የመጨረሻ የምክር ቃላት

ካናዳ ውስጥ አዲስ ሕይወት መጀመር አስደሳች ነው፤ አንዳንድ ሰዎች እንዲያውም አስቸጋሪ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ። ለመላመድ ጊዜ ይፈልጋል፤ ስለዚህ ታጋሽ ይሁኑ። እንደ እርስዎ የመሳሰሉ ብዙ አዲስ መጪዎች ተላምደው የካናዳ ኅብረተሰብ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ተቀላቅለዋል።

አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ ስራ ለመፈለግ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ የካናዳን ሕይወት ለመላመድ እንዲረዳዎ እንግሊዝኛ ወይም ፈረንሳይኛ መናገር በጣም አስፈላጊ ይሆናል። ካናዳ ከመምጣትዎ በፊት ከሁለቱ አንዱን ቋንቋ የመማር ዕድል ካጋጠመዎ የቋንቋዎን ክህሎት ለመጨመር ይረዳዎታል። ካናዳም ከገቡ በኋላ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክህሎትዎን ለማሻሻል ያሉትን ዕድሎች መጠቀም ይኖርብዎታል።

በዙሪያዎ የሚገኙ ሰዎችን ይጠይቁ። የሚያሳስብዎ ጉዳይ ካለ ለስፖንሰርዎችዎ ይንገሩ።

እርስዎን ለመርዳት የተዘጋጁ ሰዎችና አገልግሎቶች እንዳሉ ያስታውሱ።

የመጨረሻ ማስተካከያ የተደረገበት ኤፕሪል 2014